# አገርስ ነበረን!

«.. አገር - አገር ይላል.. ይሄ አገሬ-ብርቁ
(እኛም) አገር (አለን) .. እሚታይ በሩቁ..»1*
እማይገባበት ጊዜ እየጠበቁ!

አገርስ ነበረን!
ድንግል ጥቁር አፈር - ለምለም ብሩክታይት፣
የተፈጥሮ ጸጋ - አጊጦ ያስዋባት፤
የፍቅሯ ማኅተም - በልባችን ሰፍሮ፣
በየደም-ስራችን - እሚኖረን አብሮ፤
ግና ምን ያደርጋል!
ውበት አበቦቿን - በእምቡጥነት ቀጥፈን፣
ተፈጥሯዊ ሃብቷን - አባክነን አምክነን፣
እርቃኗን አቁመን - ግርማ ክብሯን ሽጠን፣
ብር እናፍቃለን - በጅ ያለ ወርቅ ንቀን።

የጀግኖች ትውልድ ውርስ - የአርነት ዓርማ፣
የተስፋዋ ምድር - የሰብዕ ዘር ማማ፣
እሱማ ነበረን! አገር የተዋበች፣
ስንቱን ቅኝ-ገዢ - ምራቁን ያስዋጠች፤
አናውቅበት ብለን - ተስማምቶ መኖሩን፣
መካፈል ተስኖን በጋራ ፍሬዋን፣
ነጠፈ ደረቀ.. - መና ባክኖ ቀረ፣
የፉክክሩ ቤት -ሳይዘጋ አደረ።

ሰላሙን ብንፈጥር - ለማምረት ብንጥር፣
ለሁሉ እምትበቃ - ልቃ እምታስመካ፣
«የዳቦ ቅርጫት» - ለመላው አፍሪካ፣
ልትሆን እምትችል - አገርስ ነበረን፤
ድፍን ልባችንን - መክፈቱን አቅቶን፣
ጭፍን ዐይናችንን መግለጡን ተስኖን፣
ከመርንባትና - የችጋሩን መዐት፣
ባለም መዝገበ-ቃል - ሥሟን አስጠራናት።

የዕልፍ-አዕላፋት - ታዛ መናኸሪያ፣
ሕብረ-ቀለም ውሁድ - የድንቅ ውበት ማያ፣
አገርስ ነበረን! - ባለታሪክ ዝና፣
ባለሸጋ ባህል - ባለቅርስ ገናና፤
«ነበርን» አምልከን - ያሁኑን እንዳናይ፣
መጪውን አሻግረን - እንዳናልም ራዕይ፣
የጅል ፖለቲካ - ሆኖብን ደንቃራ፣
እንክት አርገን በላን - የትውልድ አደራ።

EthioLion.Com

EthioLion.Com

አገርስ ነበረን!
የተመራመሩ - ባለብልሃቶች፣
ለክፉ ቀን ደራሽ - አምጣ ያፈራች፤
«መኖር አለመኖር..» - ባገር እሚኖሩ..፣
ፖለቲካ አንቋቸው - እንደወጡ የቀሩ፣
ላለም ትምህርት ቤት - ዘዴ እሚያስተምሩ፣
ሳይንስ ቴክኖሊጂ .. - ጥበብ እሚፈጥሩ...፣
መኖርስ ነበሩ!
ልባቸው ተነክቶ - ሁሌ እንደተቆጩ፣
በጨለማው ግዝፈት - እንደተበሳጩ፣
በ«ይነጋ ይሆናል» - በተስፋ እሚኖሩ፣
በመላ ዓለም ዙሪያ - እሱማ ነበሩ::

አገርስ ነበረን! ለሕዝቧ እማትመች፣
ሁሌም ለሚገሏት ቦታ እምታመቻች፤

አገር? ያውም አገር ነዋ! - እሱማ ነበረን፣
«ላም አለን በሰማይ..» - ሆኖ እንጂ የቸገረን፤

አገርስ ነበረን!
ጥንተ-ታሪክ አልፋ - የሰው ዘር መነሻ፣
ሆነን ቀረን እንጂ - ያለም መጨረሻ::

ጌታቸው አበራ
መስከረም ፳፻፩ ዓ/ም
(ሰፕቴምበር 2008)

1* ከአስቴር አወቀ ዘፈን በከፊል የተወሰደ